 *የአማራ ብሄርተኝነት ኢትዮጵያን አይጎዳም ፤*

[**Gabriel Bez**]()

***January 14 ·***

*ፍረዱኝ ! የአማራ ብሄርተኝነት ኢትዮጵያን አይጎዳም፤ አማራ ኢትዮጵያዊ ነውና ትግላችን በኢትዮጵያዊነቱ ለአማራነቱ የሚሞት ዋልታና ማገር የተሰፋ ስንቅ የነፃነት ዘብ ታጋይ አማራ ትውልድን መፍጠርና ይህ የእውነት አርበኛ አማራ ኃይል የአማራ ወጣቶችን ደህንንት፤ ህልውና ለሰላማቸው በጥንካሬና በብርታት ጉልበቱን አደራጅቶ በዘመነ ህወሃት ከፀሐይም በታች በአማራው ላይ የሚደረገውን ግፍ ማስቆም፤ በህወሃት አማራው በጠራራ ጸሐይ ተዋረደ ተደበደበ፤ በጭካኔ ተቀደደ፤ አካሉ ጎደለ በግፍ ተፈለጠ። በመሬቱ ተረገጠ።አማራው እንደ እንሰሳ ተሸለተ።በጲላጦስ አደበባይ እርቃኑን ቆመ። እንባውበግፍ ፈሰሰ፤ ሞቱን ይጠባበቃል። እግዚኦ! ፍረዱኝ! ትግላችን የተካደውንና እንዲጠፋ የተፈረደበትን "የአማራ የሰውነት ክብር" የአማራ ታሪክ፤ የአማራ እሴት፤ ባህል ወግ ፤ማስከበርና ማስመለስ ነው። አማራው አማራነቱ በኢትዮጵያዊነቱ ታሪከን ጠብቆ እንዲቀጥል አማራነቱ ለኢትዮጵያዊነቱ ኃይል መሆን ነው !!! አሁን በምድረ ኢትዮጵያ አማራዎች አንድ ሞት ብቻ አይጠብቃቸውም። ከዚያ በላይ ነው።በመርዝ ጤስ ታፍኖ ወይ መከተፍ፤ ወይ ሞቶ መቃጠል። ስለምን? ሳቅ አልተፈቀደልንም ደስታን የአማራ ለማደረግ አልታደልንም። ሁሉ አማራ እስረኛ ነው የአማራው ነፍስ ተንጠልጥላ ውላ ታድራለች። ስለምን? እግዚኦ! ፍረዱኝ ! አማራውን ለመታደግ የአገርና የወገን ሃላፊነት ሸክም ፤የመንፈስ ፅናት ፤እግዚአብሄር ፊቱን እስኪመልስልን ድረስ ፥አማራውተደራጅቶ ራሱን ለማትረፍ ዳግም ላለማልቀስ ለነፃነት መዝመት፥ ለሌሎች ነፍስን መታደግ ና በኢትዮጵያ አገራችን መዋረድን ማስቆም ነው" እናም ፤ የአማራ ብሄርተኝነት ኢትዮጵያን አይጎዳም እግዚአብሄር አቅሙን፤ ኃይሉን ግርማውን ይስጠን። አሜን።አንዱ አማራ ለሁሉም አማራ፥ ሁሉም አማራ ለአንዱ አማራ!*

***Gabriel Bez. 01/13/2018***